EthioLion

# ብዕሬ ‘እርሳስ’ ትሁን!

የጐንቻው!

**ብዕሬ አፍታ ትረፍ፤ደግሞ እርሳሴን ላንሳ፤**
ደንዳና ብራና ቀለሜን ጨረሰው፤ጥፎሽ ላያነሳ፤
በብዕር ስፈትግ፤ሞራውን ዘልቄ ቆዳውን ላሳሳ፤
እድሩ፤ሌላ ነው፤እያሙለጨለጨ፤ይህ የዱር እንሰሳ፤
ለካስ በእርሳስ ኖሯል በምላጭ በሾለው በውል እሚበሳ፤
ጠልቃ በምትሰርጸው፤ በብዕሬ ፈለግ አፍታ ተተኩሳ፤
ውስጠ-ወይራ በትር፤ልብ ያነጣጠራት እጅ ተንተርሳ፤
ባሩድ የምትተፋው፤ስላ-ተሳስላ እራሷን ከስክሳ፤
ጠፍታ እምታጠፍ ደጀን፤ማምከኛዋን በኋላዋ ጎርሳ፤
ብረት እምታስዝግ እሾሁን በእሾሁ፤በስለት ተጣርሳ፤
**እርሳስ ደመላሼ አገር ይጫርብሽ፤እጅ በእጁ እያነሳ።**

በእጇ ተንኮባችታ፤ተስላ፤ ተሹላ፤ ፍኖ እንድትቃኝ፤
ብዕሬ እርሳስ ትሁን፤ባሩድ በአፈ-ሙዟ፤እንድተፍልኝ፤
አጭሯ ‘ምርኳዜ’፤ድንገት፤ብድግ ስል፤ እንድትደግፈኝ፤
ዘወትር በቅምጥ፤በአሳር ተጣጥፌ፤ስለጣመነኝ፤
እስኪ ቀና ልበል አካል ሰውነቴ እንዲፍታታልኝ፤
ብሶቴን፤ምኞቴን፤እጅ-አፍ ተቀባብሎት፤እንዲሰምርልኝ፤
ዞትር አንጋጥጨ በጐረቤት ሰማይ፤ህልም እያየሁኝ፤
ምነው በኛ ምድር፤እየደጋገመ ጠብ-መንጃ፤አቃዥሮኝ፤
መጣፍ የማይፈታው፤ ‘በትረ-አጋንታችን’እንቅልፍ ነሳኝ፡
እስኪ ወገን ‘**አክር**’፤እርግምት ማርከሻ፤ማተብ፤አንግተኝ፤
**እሰናዘርበት፤ሱሪና፤ቡታንታ፤ቀበቶ አስታጥቀኝ።**

ብዕሬ አቤቱታ፤ለሰማይ ለምድሩ፤ስንክሳር ስትከትብ፤
ሁለት፤አሥርተ-ዓመት ተግታ ስትሰብክ፤ራዕይ ምናብ፤
አገር ቀበሌውን ድንዝዝ አቆፍኝቶት፤የፍራት ድባብ፤
ሰው በድን ይኖራል፤በመንፈስ ተራቁቶ፤ተለያይቶ ልብ፤
‘ነብዩ-ጠንቋዩ’ እያሽባበሩ፤እስር፤ጥላሞቱን እንዲያነበንብ፤
ለካስ ‘እርሳስ’ ኖሯል፤መጋረጃ እሚቀድ፤እሚበሳ፤ግንብ፤
‘በተሰላጠነው፤በተፈጣጠነው’፤‘ዘመነ-እድራችን’ የጨዋታ ደንብ፤
እኔም ልንጠራራ፤ሞረሽ ልጠራራ፤እንድሻገር፤ካብ፤
በውስጤ መሽጌ አንጀቴን ስቆፍር አካሌ እንዳይዝብ፤
ብዕሬም ትታገስ ቀለም ትቆጥብ፤አገር ረቂቁን በእርሳስ እስኪከትብ፤
ሕዝብ እጁን ያፍታታ ‘በእርሳስ መጣጥፉ’ በቃል ይናበብ፤
**ይበል በአደባባይ ድንቁርናን፤ ይጥፋ፤ ‘<u>ደደቢት፤ ደደብ</u>’።**

*አካሉን በነዲድ አጋይቶ የነፃነትና የተታደሎ ህያው ታሪክ በደሙ ጽፎልን ለተሰዋው፤፤ኢትዮጵያዊ ሰማዕት፤ አራዓያ የትግል ሻማ ለለኰሰልን ለመምህር ‘የኔሰው ገብሬ’ መታሰቢያ ትሁን.*

መልካም ‘የምዕራባዊያን’ የገና አና አዲስ ዓመት በዓል!

yegonchaw@yahoo.co.uk

Ethiopia Will Prevail!